# 4ኛ ትምህርት

ጥቅምት 5-11 2009 ዓ.ም October 15— 21

# እግዚአብሔርና የሰውልጅ ስቃይ

## ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ፡- ሮሜ 1፡18-20፣ ኢዮብ 12፡7- 10፣ ራዕይ 4፡11፣ ቆላ. 1፡16-17፣ ማቴ. 6፡34፣ ኢዮብ 10፡8-12፣ ሮሜ 3፡1-4፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ ይበቃዋል፡፡" (ማቴ. 6፡34)

ከ ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተለየ የኢዮብ መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ ከእስራኤል ህዝብና መሬት አውድ የራቀ ነው፡፡ ከዘፍጥረት አንስቶ እግዚአብሔር ለአብርሃም ‹ታላቅ ህዝብ አደርግሃለሁ› (ዘፍ. 12፡2) ብሎ ቃል ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ራዕይ ‹ቅድስቲቱ ከተማ› ኢየሩሳሌም (ራዕይ 22፡19) ድረስ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ቃል ኪዳን አውድ የእያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ቅርጽ እንዲኖረው አድርጓል፡፡

ከኢዮብ ላይ ግን ይህንን ፈፅሞ አናገኝም፤ በጥንታዊቷ እስራኤል ታሪክ ውስጥ መሠረት ስለሆነው የዘጸአት (ከግብፅ የመውጣት) ክስተት እንኳን አይጠቅስም፡፡ ለዚህ ዋነኛው ምክንያት ሙሴየኢዮብን መጽሐፍ ከዘፍጥረት መጽሐፍ ጋር አብሮ የጻፈውበምድያም ሆኖ ስለነበር ነው፡፡ (*The SDA Bible commentary, vol. 3, P. 1140ን* ይመልከቱ) ዘጸአት (የእስራኤል ከግብጽ መውጣት) ያልተጠቀሰውበዛን ወቅት ገና ስላልተከሰተ ነበር፡፡

ምናልባት ሌላም የበለጠ አስፈላጊ ምክንያት ሊኖረው ይችላል። የኢዮብ መጽሐፍ ዋነኛ ፍሬ ሀሳብ የሆነው የሰው ልጆች ስቃይ ዓለምቀፋዊ ነው። ለተወሰኑ ህዝቦችና ለሆነ ጊዜ ብቻ የተመደበ አይደለም። አይሁድ ይሁን አህዛብ ከኢዮብ ሀዘን የምንገነዘበው በወደቀው አለም ውስጥ ስቃይ ስለመኖሩ ነው። ምንም እንኳን የእርሱ ህመም የተለየ ቢሆንም የእኛን ስቃይ ወክሎ ቀርቧል።

**የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለጥቅምት 12 ሰንበት ይዘጋጁ።**

*እሁድ ጥቅምት 6* *October 16*

## እግዚአብሔር በተፈጥሮ ውስጥ

**ሮሜ 1፡18-20 ያለውን አንብቡ። ጳውሎስ ምን እያለን ነው ያለው?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

አስደናቂ አረፍተ ነገሮች ናቸው። የእግዚአብሔር መኖርና እውነታነት በበቂ ሁኔታ ‹በተፈጠሩ ነገሮች› አማካኝነት ተገልጧል፤ ስለዚህ እነዚያ ህዝቦች ላለማመናቸው ‹ማመካኛ የላቸውም›። ጳውሎስ እያለን ያለው ከፍጥረት ብቻ የሰው ልጆች በአጥጋቢ ሁኔታ ስለ እግዚአብሔር መኖርና ባህሪ በመማር በፍርድ ቀን በእውነተኛ ሚዛን ሊኮነኑ እንደሚገባ ይረዳሉ።

ያለምንም ጥያቄ ተፈጥሮ ስለ እግዚአብሔር መኖር ብዙ የሚገልጽልን ነገር አለው። ከ3000 ዓመታት ወዲህ ከነበሩት አባቶች ከ300 ዓመታት በፊት የነበሩት አባቶች መገመት እንኳን የማይችሉትን ዘመናዊው ሳይንስ አስደናቂ ስለሆነው ተፈጥሮ በዝርዝር ገልጧል። እዚህ ጋር አንድ አስደናቂ የሆነ ምጸት እናገኛለን፡ በህይወት ውስጥ ያለው ሁኔታ ውስብስብ እንደሆነ ሳይንስ የበለጠ ባወቀ ቁጥር የተፈጥሮ መነሻ (origin) ድንገት የመጣ ወይም አጋጣሚ ነው ማለቱን እየቀነሰ ይሄዳል።

የአይፎን የሞባይል ቀፎ ለምሳሌ የሚመስለው መጀመሪያ የታቀደለትን ቅርጽ ነው፣ የሚተገበረው

በታቀደለት የአሰራር መንገድ ነው፣ ከውስጥም ከውጭም የታለመለትን እቅድ ያንጸባርቃል፤ የሚሰራውም በታቀደለት ንድፍ ብቻ ስለሆነ አስቀድሞ በንድፍ እንደተሠራ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ የታቀደለትን

ንድፍ እየመሰለ፣ ተግባሩ እንደ ንድፉ ሆኖ ከውስጥም ከውጪም የራሱን ንድፍ እያንጸባረቀ የሚሰራውም በንድፉ አማካኝነት ሆኖ ይህ በአጋጣሚ እየሆነ እንዳለ ይታመናል፡፡ የሚያሳዝነው ብዙ ሰዎች ይህንን ኃሳብ በማመን ተታለዋል፡፡

**ኢዮብ 12፡7-10ን አንብቡ፡፡ እነዚህ ቃላት በሮሜ 1፡18-20 ላይ የተገለፁትን ሃሳቦች**

**እንዴት ይገልጻሉ?**

---

---

እዚህ ጋ ለእኛም እንደተነገረን የእግዚአብሔር እውነታነት በተፈጠረው አለም ላይ ተገልጧል፡፡ በውድቀት ውስጥ ሆኖ ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ባህሪ በሙላት መግለጽ ባይችልም የመፍጠር ሃይሉንና የእርሱን በጎነት በትክክል እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

**በተለየ ሁኔታ ለእርስዎ የእግዚአብሔርን ሀይል እና በጎነት የሚነግርዎት የትኛው የተፈጥሮ ክፍል ነው? ያገኙትን መልካም መልዕክት በመውሰድ ጥንካሬንና ብርታትን ማግኘት የሚችሉት እንዴት ነው?**

*ሰኞ ጥቅምት 7* *October 17*

## ምንም ነገር ከራሱ አልመጣም

ከእግዚአብሔር መኖር ጋር በተያያዘ ብዙ መልካምና ጠንካራ ክርክሮች አሉ፡፡ ከተፈጠረው አለም ምስክርነት በዘለለ ሰፊውን ዩኒቨርስ ማዕከል ያደረገ ኮስሞሎጂካል (*cosmological*) የሚባል ክርክርም አለ፡፡ በዋነኛነት ሀሳቡ ምንም ነገር በራሱ ሊመጣ ወይንም ምንም ነገር ራሱን ሊፈጥር አይችልም የሚል ነው፡፡ በዚህ

ፈንታ ግን የተፈጠረው ነገር በሌላ ነገር ተፈጥሮአል። የተፈጠረው ነገር በሙሉ ቀድሞ የተፈጠረው በሌላ አካል ነው። ይህ ሂደት ይቀጥል ይቀጥልና ያልተፈጠረና ሁሌ የሚኖር አካል ጋ ይደርሳል። ያ ማን ሊሆን ይችላል? ቃሉ እንደሚያረጋግጠው እግዚአብሔር ነው።

**የሁሉ ነገር መነሻ ምን እንደሆነ የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ያስተምሩናል?**

ራዕ. 4፡11

___

ቆላ. 1፡16-17

___

ዮሐ. 1፡1-3

___

እነዚህ ጥቅሶች ስለ ፍጥረት አመጣጥ ትክክለኛና አሳማኝ በሆነ መንገድ ፈጣሪያቸው ዘላለም ነዋሪው እግዚአብሔር መሆኑን ይገልጻሉ። አንዳንድ ጠበብቶች የእግዚአብሔርን መኖር ስለሚቃወሙ ሌላ አማራጭ ሀሳብን ይዘው መጥተዋል። ሃያልና ዘላለማዊው አምላክ ዩኒቨርስን ፈጠረ በማለት ፈንታ ይህችን አለም የፈጠራት ምንም ነገር የለም ይላሉ። እንደ ስቴፈን ሀውኪንግ ያለ ታዋቂ ሳይንቲስት አይዛክ ኒውተን ቀድሞ ይዞት የነበረውን መንበር አሁን ላይ የተቆናጠጠ ሰው ዩኒቨርስን የፈጠረው ‹ምንም ነገር› የለም ብሎ ይሞግታል።

‹‹ምክንያቱም እንደ ስበት ህግ ያሉ ህጎች ስላሉ አለማችን ከምንም ነገር ራስዋን መፍጠር ትችላለች።›› *Stephen Hawking and Leonard Mlodinow, The Grand Design (New York: Random House, 2010), p. 180.*

ምንም እንኳ ሃውኪንግ ሀሳቡን ለመግለጽ ጥልቅና ውስብስብ ሂሳባዊ ስሌቶች ቢኖሩትም አንድ ሰው መልካም የሚባለው ሳይንሳዊ የለውጥ ሂደት የጀመረው ከ400 ዓመታት በፊት መሆኑን ሲረዳና ዝነኛ የሆነው ሳይንቲስት ዩኒቨርሳችን የመጣችው ከምንም ነው ብሎ ሲሞግት መስማት ያስደንቀዋል። በታላቅ

ሳይንቲስት የተነገረ ቢሆንም እንኳን ስህተት ስህተት ነው፡፡

**ከዚህ አውድ አንጻር 1ኛቆሮ. 3፡19ን ያንብቡ፡፡ ለምንድነው ክርስቲያኖች ይህንን አስፈላጊ እውነት ሁልጊዜ መጠበቅ ያለባቸው?**



## ከመጽሐፎች ሁሉ ጥንታዊው

በእግዚአብሔር ከማያምኑ ሰዎች ግነት በተቃራኒ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ለእምነታቸው ማረጋገጫየሚሆኑ አያሌ ምክንያቶች አሏቸው፡፡ ስለአለማመናቸው ምክንያት የሚሆን ለዘመናት ሲከሰት የኖረ ችግር አለ፤ ይህም ደግሞ የሰው ልጆች ስቃይ እና ክፋት መኖር ነው፡፡ እግዚአብሔር መላ እሱነቱ መልካም፣ አፍቃሪ እና ሀያል ከሆነ እንዴት ክፋት ሊኖር ቻለ? ይህ ለብዙዎች የመሰናከያ ድንጋይ ሆኗል፡፡

**እውነት ከተናገርን የእግዚአብሔርን መኖርና ፍቅር ከተለማመዱ ታማኞች አንዳንድ ጊዜ እንደዚህ አይነት ሞጋች ጥያቄዎችን ያልጠየቀ ማን አለ?**

ኤለን ጂ. ኋይትም የአይሁድ የቀድሞ ባህል የሚያስተምረውን የኢዮብን መጽሐፍ ሙሴበምድያም ሆኖ መፃፉን ማስተማሯ እጅግ ያስገርማል፡- ‹‹ጭር ባለው በረሀ ውስጥ ከረጅም አመታት በፊት ሙሴ ለታላቅ ሥራ የመዘጋጀት እድል ብቻ አልነበረም ያገኘው፡፡ በዚህ ጊዜ ግን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ዘፍጥረትንና የኢዮብን መጽሐፍ ጻፈ፤ይህም በእግዚአብሔር ሕዝቦች ዘንድ እስከ ዘመን ፍጻሜ በጥልቅ ፍላጎት የሚነበብ ክፍል ሆነ፡፡›› *Ellen G. white comments, the SDA Bible commentary, vol. 3, p. 1140.*

ይህ የሚነግረን ከመጀመሪያዎቹ ሁለት መፅሐፎች አንዱ የሆነው የኢዮብ መጽሐፍ ዓለምቀፋዊ ጉዳይ ስለሆነው ስለ ሰው ልጅ ህመምና ስቃይ ማተቱን ነው፡፡ ይህም ማለት እግዚአብሔር ጉዳዩ ለሰብአዊ ዘር

ሁሉ ትልቅ ጥያቄ እንደሚሆን ቀድሞ አውቋል፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ የኢዮብን ታሪክ ሙሴ እንዲጽፍ ያደረገው ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ብቻችንን በስቃይና ህመም እንዳልተወን፣ እርሱ ከኛ ጋር እንደሆነ፣ ሁሉንም ነገር እሱ እንደሚያውቅና በስተመጨረሻም ነገሮቻችንን በመልካም እንደሚያቃናልን ተስፋ እንዳለን አስቀድሞ አሳወቀን።

**የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ክፋት እውነታነት የሚያስተምሩን ምን ነገር አለ? ማቴ. 6:34፣ ዮሐ. 16:33፣ ዳን. 12:1፣ ማቴ. 24:7።**

---

ከክፉው በኩል በእግዚአብሔር መኖር ዙሪያ ያለው ሙግት ሊስተዋል የሚችል ቢሆንም ከእግዚአብሔር ቃል ብርሃን አንጻር ስናይ ትርጉም አይሰጥም። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉን ስለሚያውቅ፣ ሐያልና አፍቃሪ ስለሆነው አምላክ መኖር ቢያስተምረንም ስለ ክፋት፣ ስለ ሰው ልጅ ስቃይ እና ሀዘን መኖርም ያስተምረናል። የክፋት መኖር በእግዚአብሔር ላለማመን ሰበብ አይሆንም።

በፍጥነት የኢዮብን መጽሐፍ ስናነብ በዛ አስቸጋሪ ወቅት ቢያልፍም ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር መኖር ፈጽሞ አልጠየቀም። በዚህ ፈንታ ግን በእርሱ ላይ ይህ ሁሉ ችግር ለምን እንደደረሰበት ጥያቄ አቀረበ።

**በሚያጋጥመን ክፋት ላይ ጥያቄ ማንሳት ተፈጥሮአዊ ነገር ነው። ምንም ያህል ክፋት ቢኖር በእግዚአብሔር መልካምነት ላይ መታመንን የምንማረው እንዴት ነው?**

## አጣብቂኝ

**ከኢዮብ መጽሐፍ ላይ ቀጣዮቹን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ኢዮብ ከምን ጉዳይ ጋር ነው እየተሟገተ ያለው? ያልጠየቀውስ ጥያቄ ምንድነው? ኢዮብ 6፡4-8፣ ኢዮብ 9፡1-12፡፡**

---

---

በትናንቱ ጥናታችን እንደተገለጸው ስለ እግዚአብሔር የመኖር ጉዳይ በኢዮብ መጽሐፍ ላይ ሲነገር አናገኝም፡፡ በዚህ ፈንታ ጥያቄው ኢዮብ በእንደዚህ ያለ መከራ ውስጥ ለምን ያልፋል? የሚል ነው፡፡ በእርሱ ላይ የሆነውን ነገር ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በተለይ በእግዚአብሔር መታመኑ ሲታሰብ የተነሳው ጥያቄ ተገቢ ነው፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው በእግዚአብሔር የማያምን ሆኖ ችግር ቢመጣበት በአንጻራዊነት ምላሹ ሊሆን የሚችለው ቀላልና ቀጥተኛ ነው፡፡ የምንኖረው ትርጉም አልባ፣ አላማ቎ቢስ በሆነና ማንም ግድ በማይለው አለም ውስጥ ነው ይላል፡፡ ስለዚህ ከባድ፣ መጥፎና ለኛ ግድ በሌለው የተፈጥሮ ኃይል ተከበን አንዳንዴ አላማ ቢስ በሆኑ

ችግሮች ሰለባ መሆናችን ይታያል፡፡ ህይወት ራስዋ አላማ ቢስ ሆና ከቶየች ከህይወት ጋር ያሉ መከራዎችስእንዴት ትርጉም አልባ አይሆኑ?

ብዙዎች ይህ መልስ አጥጋቢ ያልሆነና ተስፋ የለሽ ቢሆንባቸውም በእርግጠኝነት እግዚአብሔር የለም ብሎ ለሚያምን ሰው ትርጉም ይሰጣሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን እንደ ኢዮብ ላለ ሰው የደረሰበት አጣብቂኝ የተለየ ነው፡፡

**ኢዮብ 10፡8-12ን ያንብቡ፡፡ ኢዮብ እየተሟገተበት ያለበትን አስጨናቂ ጥያቄ እንድናስተውል ይህ ጥቅስ**

**እንዴት ያግዘናል?**

አዎን ኢዮብ እየተሟገተበት ያለው ጥያቄ አያሌ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎችም እስከ አሁን ድረስ እየተሟገቱበት ያለ ጥያቄ ነው፤ መልካምና አፍቃሪው እግዚአብሔር ካለ ሰብአዊ ዘር በሙሉ ለምን በእንዲህ አይነት ሁኔታ ይሰቃያል? እንደ ኢዮብ የመሰሉ ‹መልካም› ሰዎች ምንም ዋጋ በማያመጣላቸው ችግርና መከራ ውስጥ ለምን ያልፋሉ? በድጋሚ ዩኒቨርሳችን እግዚአብሔር የሌለባት ከሆነች መልሱ፡- ቁሳዊ በሆነው ዩኒቨርስየአቶሞችና ሞለኪውሎች ድንገተኛ ውጤት የሆኑሰዎች በሚኖሩባት አለም ይህ የሚጠበቅ ነው የሚል ይሆናል፡፡

ኢዮብ ግን ከዚህ የተሻለውን ነገር ያውቃል፤እኛም እንደዛው፤ አጣብቂኙ ይህ ነው፡፡

*ሐሙስ ጥቅምት 10* *October 21*

## የእግዚአብሔር መልካምነት በጥያቄ ውስጥ (ቲዎዲሲ)

**ሮሜ 3፡1-4ን ያንብቡ፡፡ ምንም እንኳን የመነሻ አውዱ የሚያወራው ታማኝ ስላልሆኑት አንዳንድ የቃል ኪዳን ህዝቦች ቢሆንም ጳውሎስ እየነገረን ያለው ትልቁ ጉዳይ ምንድን ነው? ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔር እየተናገረ ያለው ነገር ምንድነው?**

ከመዝ. 51፡4 ላይ በመጥቀስ ጳውሎስ ጌታ ራሱ "ከቃልህ የተነሳ እውነተኛ በፍርድም ፊት ረቺ" (ሮሜ 3፡

4) ስለመሆኑ ይናገራል። ሀሳቡ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተገልጾ የሚገኝ ነው። ይህም የእግዚአብሔር መልካምነት (ቲዎዲሲ) ሲሆን በክፋት ፊት የእግዚአብሔርን መልካምነት የማስተዋል ጥያቄ ነው። ይህን ሳምንት ሙሉ የምናየው ይህን እድሜ ጠገብ ጥያቄ ነው። ታላቁ ተጋድሎም ሙሉ በሙሉ በዚህ ዙሪያ ነው። በዓለም ላይ ክፋት ቢኖርም በሰው ልጅ፣ በመላእክትና በዩኒቨርስ ፊት የእግዚአብሔር መልካምነት ይገለጣል።

‹‹ረጅም ጊዜ ባስቆጠረው ተጋድሎ ውስጥ የእያንዳንዱ እውነትና ስህተት ጥያቄ አሁን ግልጽ ብሎ ተስተውሏል። የአመፅ ውጤትና የመለኮትን ደንብ ወደ ጎን የመጣል ፍሬ ለተፈጠሩ ፍጡራን በሙሉ ፍንትው ብሎ ታይቷል። ከእግዚአብሔር መንግስት በተፃራሪ የቆመው የሰይጣን አመራር ለመላው ዩኒቨርስ በግልጽ ታየ። ሰይጣን የራሱ ተግባሮች ራሱን ኮነኑት። የእግዚአብሔር ጥበብ፣ ፍትሃዊነቱና መልካምነቱ ሙሉ በሙሉ ተረጋገጠ። በታላቁ ተጋድሎ ውስጥ ያደረገው ነገርለህዝቦቹ ባለው ዘላለማዊ ክብርና በፈጠረው አለም ውስጥ ባለው መልካምነቱ የሚመራ መሆኑ በጉልህ ታየ።› *Ellen G. White, TheGreat Controversy, pp. 670, 671.*

በአለም ሀጢያት እና ስቃይ ውስጥ ጠልመን ላለን ለኛ ይህንን ማስተዋል ከባድና አዳጋች ቢሆንም (ለኛ የዚህን ያህል ከባድ ከሆነ ለኢዮብ ምን ያክል እንደነበረ እስቲ ይገምቱ) ሁሉም ነገር ሲያበቃ እግዚአብሔር በሰው ልጆች፣ በሰይጣንና በኃጢያት ላይ ያደረገው ነገር ሁሉ መልካም፣ ፍትሃዊ፣ በፍቅር የተሞላና ትክክለኛ መሆኑን እናስተውላለን። ያ ማለት ግን በአለም ላይ የሆነው ነገር ሁሉ መልካም ነው ማለት አይደለም፤ እውነታው ሁሉም ነገር መልካም አይደለም። እግዚአብሔር ግን እጅግ በተሻለው መንገድ ነገሮችን እያስኬዳቸው ነው ማለት ነው፤ ከዚያም በኃጢያት አማካኝነት የመጣው ከባድ ልምምድ ሲያልፍ እኛም ‹ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ ሆይ ስራህ ታላቅና አስደናቂ ነው፤ የዘመናት ንጉስ ሆይ መንገድህ ጽድቅና እውነት ነው› (ራዕይ 15:3) ብለን እንጮሃለን።

**አሁን በከባድ ችግር መሀል ሆነን እንኳን እግዚአብሔርን የማመስገን አስፈላጊነቱ ምንድነው?**

## ተጨማሪ ሃሳብ

ሲ.ኤስ. ሉዊስ የተባለ የክርስቲያን ፀሀፊ በመጽሐፉ ላይ ስለ ሚስቱ መሞትና ለዚህም ጉዳይ የተሟገተበትን ጥያቄ እንዲህ አስፍሯል፡፡ ‹አደገኛው ነገር (እንደማስበው) በእግዚአብሔር ማመንን ማቆም አይደለም፡፡ ትልቁ አደገኛ ነገር ስለ እግዚአብሔር እያመንኩት የመጣሁት አስቀያሚ ነገር ነው፡፡ የደረስኩበት መጥፎ ድምዳሜ ‹እግዚአብሔር የለም› ሳይሆን ‹እግዚአብሔር በርግጥ ይህንን ይመስላል› ማለቴ ነው፡፡ ራስዎትን አያታልሉ፡፡›› *A Grief observed, pp. 6, 7* ኢዮብ እየተሟገተበት ያለው ጥያቄም ይህ ነው፡፡ እንደተመለከትነው እርሱ የእግዚአብሔርን መኖር አልተጠራጠረም፤ የእርሱ ሙግት ከእግዚአብሔር ባህሪ ጋር የተያያዘ ጥያቄ ነው፡፡ ኢዮብ በታማኝነት ጌታውን አገልግሎአል፡፡ ኢዮብ ‹መልካም› ሰው ነበር፡፡ የደረሰበት ነገር በሙሉ እንደማይገባው አውቋል፡፡ ስለዚህ በሀዘን ውስጥ ሆነው በእግዚአብሔር የሚያምኑ

አያሌ ሰዎች የሚጠይቁትን ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔር በርግጥ ምን ይመስላል? ይህ በርግጥ የታላቁ ተጋድሎ ይዘት አይደለምን? ጥያቄው ያነጣጠረው በእግዚአብሔር መኖር ላይ ሳይሆን በባህሪው ላይ ነው፡፡ ታላቁን ተጋድሎ ወደ ፍፃሜ የማምጣት ሂደት ብዙ ነገርችን የያዘ ቢሆንም የየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ‹ክርስቶስ እንደ ወደደን ራሱንም ስለኛ መልካም መአዛ ያለው መባና መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር እንደሰጠ› (ኤፌ. 5፡2) ለዩኒቨርስ በሙሉ የፈጣሪያችንን እውነተኛ ባህሪ ከምንም ነገር በላይ የገለፀ መሆኑ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ መስቀሉ እግዚአብሔር የምንተማመንበት አምላክ መሆኑን ያሳየናል፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ ሰዎች ስቃይ ሲደርስባቸው ስላለው ሁኔታ ላይ ያተኩሩ። ሀዘን ሲገጥማቸው በእግዚአብሔር መኖር የሚያምኑ ሰዎች የሚጠይቁትን ጥያቄ በመጠየቅ አይሟገቱም። በሌላ በኩል መፍትሄን ለማግኘት ያላቸው ተስፋ ምንድነው? እስቲ አስቡ በዚህ አለም ላይ የሚያጋጥመንን ነገር ሁሉ አልፈን መጨረሻችን ግን ምንም ሳይሆን መቃብር ሲሆን፤ አያሌ በእግዚአብሔር መኖር የማያምኑ ሰዎች ከህይወት ጽልመት የተነሳ ለህይወት ትርጉም ቢያጡ እምብዛም አይገርምም። የሊቃውንት ስነ ጽሁፎች ህይወት ምን ያህል ትርጉም አልባ እንደሆነች በሚገልጹ ማብራሪያዎች የተሞሉናቸው። እኛስ በከበበን ሀዘን ውስጥ ሆነን አስቸጋሪ ጥያቄዎች ቢኖሩንም ከእምነታችን ተስፋን አንግበን መጓዝ የምንችለው እንዴት ነው?

2. አሁን ላይ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ባህሪ በጉልህ ሁኔታ በገለፀልን መስቀሉ ላይ ማተኮራችን ምን ያህል አስፈላጊ ነው? በሀዘን፣ በክፉ ሀይል ስንጎዳ መስቀሉ ስለ እግዚአብሔር ባህሪ ምን ይነግረናል? አሁን ላይ ዛሬ እየገጠመን ካለው ሁኔታ በመነሳት የመስቀሉን እውነታነት ከፊት ለፊታችን በማየት ተስፋን ልንሰንቅ የምንችለው እንዴት ነው?